DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS



# የወላጅ - መምህር ስብሰባ የማገናዘቢያ ዝርዝር

(Parent-Teacher Conference Checklist)

**ከስብሰባው በፊት**

- ☐ ከልጅዎ ጋር ተነጋገሩ። "ስለ ትምህርት ቤት ምን ይሰማኻል?" "በትምህርት ጥሩ የምታከናውነው ነገር ነገር ምንድን ነው?" "በትምህርት ቤት የበለጠ እርዳታ በነበረኝ ብለህ የምትለው ነገር ምንድን ነው?"
- ☐ የልጅውዎን የቤት ሥራ፣ ፈተናዎችን መገምገም፣ እና ከስብሰባው በፊትም ከመምህሩ ጋር ጋር ግንኙነት ማድረግ። ስለ ልጅዎ ጥንካራ እና ደካማ ጎኖች በሚገባ ተረድተው ጠንካራ መረጃ ይዘው ስብሰባው ላይ ይገኙ።
- ☐ ለመምህሩ ሊያነሷቸው የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች ዝርዝር ይጻፉ። እዚህ ላይ ነገሩን ለመጀመር የሚረዱዎት ጥቂት ምሳለዎች ቀርቦልዎታል።
    - "ልጄ በትምህርቱ ከቀሩት የክፍል ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር የትምህርት አከናወኑ ሁኔታ ከምን ደረጃ ላይ ነው?"
    - "ልጄ ጥሩ የሠራውን እና እሱ/እሳ የታገለበትን/ችበትን የቤት ሥራ ማየት እችላለሁ?"
    - "ከቤት ትምህርት እንዲማር ማድረግ ያለብኝ ድጋፍ ምንድን ነው?"
    - "ልጄን በትምህርት ቤት ለመደገፍ እና የሚጠበቅበትንም ውጤት ለማምጣት በትምህርት ቤት ምን ምን አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች ነው ያሉት ?"

**በስብሰባው ወቅት**

- ☐ ወደ ስብሰባ ቀና በሆነ በጥሩ መንፈስ ይምጡ፣ ስለ ልጅዎ ያለዎትን አሳሳቢ ጉዳዮች እና እንዲሁም ተስፋዎች ቀና፣ ግልጽ፣ እና ሀቀኝነት ይኑርዎት።
- ☐ .ስብሰባዎች ባለሁለት ዘርፍ (two-way) ውይይቶች ናቸው። መምህሩ ስለ ልጅዎ ከትምህርት ክፍል ውጭ ከእርስዎ ለመስማት ይፈልጋል። ለምሳሌ፣ ልጅዎ ስለሚደሰትባቸው ተግባራት እና ክንዋኔዎች እንዲሁም ልጅዎ በሚደሰትባቸው ተግባራት እና ክንዋኔዎች እና እንዲሁም ልጅዎ በቅርብ ጊዜ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ስላሳየቸው ለውጦች ጉዳይ ለመምህሩ ለመግለጽ ይሞክሩ።
- ☐ ድንገት የጊዜ እጥረት ከገጠመ እጅግ መቅረብ የሚገባቸውን ጥይቄዎች ብቻ ይጠይቁ።
- ☐ ከልጅዎ መምህር ጋር አንድ ዐይነት ቋንቋ የማይነገሩ ከሆነ በስልክ የ ቋንቋ ትርጉም አገልግሎት ( language line) ለመጠቀም ይጠይቁ፡፡ በስልክ የ ቋንቋ ትርጉም አገልግሎት ( language line) የ 24 ሰዓት የ ቋንቋ ትርጉም አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ አገልግሎቱ ወዲያውኑ ይገኛል።።

**ከስብሰባው በኋል**

- ☐ እቅድ ያውጡ። ልጅዎን ለመርዳት ምን እንደሚያደርጉ እና ምን ያህል ጊዜስ ደጋግመው እርዳታ እንደሚያድርጉት ይጻፉ።
- ☐ ከመምህሩ ጋር እንደገና የሚገናኙበትን ቀን ቀጠሮ ያሲዙ። እንዴት እንደሚገናኟቸው እና እነሱም እንዴት እንደሚያገኙዎት (ስልክ፣ ኢሜይል፣ ቴክስት ወዘተ) የመሰለውን ይግለጹ።
- ☐ ስብሰባው እንዴት እንደተካሄድ እና ምንስ ትምህርት እንዳገኙበት ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩበት። በተግባር እቅድዎ ላይም የልጅውን አስተዋጽዖ ይጠይቁት።

Sources: Harvard Family Research Project and National PTA